የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia

# በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ የመኖሪ ቤት መግዣ/መሥሪያ የቁጠባ ሂሣብ እና ብድር

# (Diaspora Mortgage Saving Account and Mortgage Loan)

## 1. አጠቃላይ ይዘት

- ይህ ሂሣብ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት መግዣ/መሥሪያ ብድር ከባንኩ እንዲያገኙ የሚያስችል የብር የቁጠባ ሂሳብ ነው፡፡
- ወደዚህ ሂሣብ ገቢ ማድረግ የሚቻለው ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የውጭ አገር ገንዘቦች ብቻ ነው፤
  - ✓ የአሜሪካን ዶላር
  - ✓ የእንግሊዝ ፓውንድ
  - ✓ ዩሮ
- ከውጭ አገር የተለያዩ የገንዘብ ማስተላለፊያ ዘዴዎችን በመጠቀም ወደተከፈተው ሂሣብ ገንዘብ በቀጥታ ገቢ ማድረግ ይቻላል፡፡
- በጥሬ ገንዘብ ገቢ ለማድረግ የውጭ ምንዛሪው ወደአገር ሲገባ በጉምሩክ በኩል የተመዘገበበትን የገንዘብ ዲክላራሲዮን በማስረጃነት ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡
- ወደተከፈተው ሂሣብ ተቀማጭ የሚሆነው ገንዘብ በዕለቱ ባለው የውጭ ምንዛሪ መጠን ተሠልቶ ወደ ብር ተቀይሮ ተቀማጭ ይሆናል፡፡
- በዚህ ሂሣብ ላይ መደበኛው የተቀማጭ ሂሣብ የወለድ መጠን ይከፈላል፡፡
- ከዚህ ሂሣብ በማንኛውም ጊዜ በብር በከፊል ወይም በሙሉ ወጭ ማድረግ ይቻላል፡፡

## 2. የብቁነት መስፈርቶች

የዚህ ሂሣብ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት፣

- ➢ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን፣
- ➢ በውጭ አገር የሚኖሩ በትውልድ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ አገር ዜጎች፣
- ➢ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው ነገር ግን በሥራ ምክንያት በውጭ አገር ከአንድ ዓመት በላይ የኖሩ እና የሚኖሩ ለዚህም በቂ ማስረጃ ሊያቀርቡ የሚችሉ ናቸው፡፡

3. ሂሳቡን ለመክፈት የሚስፈልጉ ሠነዶች

- በትክክል የተሞላ እና በሂሣብ ከፋቹ ወይም በወኪሉ የተፈረመ የሂሳብ መክፈቻ ማመልከቻ ቅጽ፣
- ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት፣
- በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሠዱበት አገር ፓስፖርት እና የትውልደ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ፣
- የመኖሪያ ወይም የሥራ ፈቃድ
- የሂሳብ ከፋቹ አንድ የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ
- ሂሳቡ በወኪል የሚከፈት ከሆነ የተወካዩ ፎቶግራፍ፣ የውክልና ሰነድ እና የመታወቂያ ካርድ

4. የሂሳቡ አከፋፈት ሁኔታ

- በግንባር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ
- በግንባር መቅረብ የማይችሉ አመልካቾች ማንነታቸውን ለማረጋገጥ በየአሉበት አገራት ባሉ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች እና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች
- ህጋዊ የውክልና ስልጣን የተሰጣቸው ግለሰቦች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች በመቅረብ በወካያቸው ስም ይህንን ሂሣብ መክፈት ይችላሉ፡፡

5. በውጭ አገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀ የመኖሪያ ቤት መግዣ/መሥሪያ ብድር (Diaspora Mortgage Loan) አጠቃላይ ይዘት

- ይህ ብድር ለመኖሪያ ቤት መግዣ/መሥሪያ የሚውል ነው፡፡
- ማንኛውም ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ዳያስፖራ የብድር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
- የብድር ጥያቄ ሲቀርብ አመልካቹ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ወይም መግዣ ዋጋውን ቢያንስ 20 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ማስገባት ይኖርበታል፡፡
- ባንኩ የሚሰራውን ወይም የሚገዛውን የመኖሪያ ቤት ዋጋ እስከ 80 በመቶ ያበድራል፡፡
- ብድሩ በአሜሪካን ዶላር፥ በእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በዩሮ መከፈል ይኖርበታል፡፡
- የብድር ጥያቄ ሲቀርብ የሚከተሉት ሰነዶች መሟላት ይኖርባቸዋል፤
    - የመኖሪያ ወይም የሥራ ፈቃድ
    - ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊነት ፓስፖርት፣